# የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ

## *ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ማወቅ ያለባቸው ነገር*

### ***ደንቡ ላይ የተደረጉ ለውጦች IKA-RA የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ*** **ከትምህርት አመት 2026-2027 ጀምሮ**

MCPS ለተማሪዎችና ለቤተሰቦች የበለጠ ወጥነትና ግልጽነት እንዲኖረው ለማድረግ የትምሕርት ውጤት አሰጣጥና የሪፖርት አቀራረብ አሠራሮችን ለውጥ አድርጓል። እነዚህን የሚጠበቁ ነገሮች ማወቅ ተማሪዎች በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዙ እና ስለ ስራቸው በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲያደርጉ ሊረዳቸው ይችላል፣ እንዲሁም ለቤተሰቦች የተሻለ መረጃ ይሰጣል። ማወቅ ያለብዎት ቁልፍ ለውጦች እነሆ።

**የማስረከቢያ ቀናት እና የጊዜ ገደቦችን በሚመለከት –** ለተማሪዎች የቤት ስራዎች ሲሰጣቸው ተማሪዎች እና ወላጆች ግንዛቤ እንዲኖራቸው የመጨረሻ ማስረከቢያ ቀኖችን እና የጊዜ ገደቦችን በግልጽ ያሳያሉ። **ለምሳሌ፡- DNA ምዘና (መቅረብ ያለበት ጊዜ: 4/20, የጊዜ ገደብ: 4/27)**

**የጊዜ ማራዘም አኮሞዴሽን ማብራሪያ –** IEP፣ 504 ዕቅድ ወይም EML ዕቅድ የጊዜ ማራዘም የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች **የማጠናቀቂያ ቀን እና የጊዜ ገደብ እንዲኖር ይደረጋል።**

**ከትምሕርት ቤት መቅረት ጋር በተያያዘ ምክንያት የሚደረግ የማካካስ ስራ – ህጋዊ ፍቃድ አግኝተው ከት/ቤት የቀሩ ተማሪዎች ሲመለሱ ያመለጣቸውን የትምህርት ስራ እንዲያካክሱ ይፈቀድላቸዋል።** መምህራን ተመጣጣኝ የሆነ ግን የተለየ የትምሕርት ሥራ ወይም ምዘና ሊሰጧቸው ይችላሉ። **ያለ ፈቃድ ከክፍል ወይም ከትምህርት ቤት ሆን ብለው የሚቀሩ ተማሪዎች መቅረታቸው በርዕሰመምህር ወይም በተወካዩ የተረጋገጠ ከሆነ ያመለጣቸውን የትምሕርት ስራ ለማካካስ ብቁ አይሆኑም።**

**ዘግይቶ የሚቀርብ የትምህርት ስራ –** ዘግይቶ የሚቀርብ የትምህርት ስራ **የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ** ተቀባይነት አይኖረውም። አዲስ ውጤት የተሰጠባቸው የቤት ሥራዎች እና የትምህርት ግምገማዎች **በማርክ መስጫ ወቅት እስከ መጨረሻዎቹ አምስት የትምህርት ቀናት** አይሰጡም። በዚህ ጊዜ ውስጥ ትምሕርት ይቀጥላል።

**ለመልመጃነት የሚሰጥ የቤት ስራ እና ዝግጅት–** ለልምምድ እና ለዝግጅት የተመደበ የቤት ስራከማርክ መስጫ ወቅትየትምህርት ውጤት **10%** የሚቆጠር ሲሆንበማጠናቀቂያ የትምህርት ውጤት ላይ ይደመራል።

**የአንድ ጊዜ ሥራ ውስንነት –** የአንድ ጊዜ የትምህርት ሥራ ምደባ ወይም ግምገማ **ከተማሪ የማርክ መስጫ ወቅት ውጤት 20%** OF በላይ ሊቆጠር አይችልም ይህ ቀድሞ ከፍተኛ 25% ከሚባለው የሚቀንስ ነው።

**ወጥነት ያለው እና እንደገና ምዘና የመውሰድ እድሎች –** ተማሪዎች **በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት** በአስተማሪዎቻቸው እውቅና ከተሰጣቸው ድጋሚ የትምሕርት ምዘና/ፈተና ለመውሰድ ቢያንስ ሁለት እድል ሊኖራቸው ይችላል። ተገቢነት ያላቸው የቤት ሥራዎች **"R" ምልክት ተደርጎባቸው** StudentVue እና ParentVUEይታያሉ። ተገቢ ከሆነ እንደገና ትምሕርት ሲሰጥ መሳተፍ ያስፈልጋል።

**ስለ AI አጠቃቀም እና የአካዳሚክ ተአማኒነት የሚጠቅ መስፈርት –** ትምሕርት ለመማር እና የቤት ሥራዎችን ለመሥራት **አርተፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) መቼ እና እንዴት መጠቀም እንደሚኖርባቸው መምህራን** ለተማሪዎቻቸው ይገልጹላቸዋል። ያልተፈቀደ AI አጠቃቀም ሐቀኝነት የጎደለው አካዳሚክ ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። መምህራን ተማሪዎች የትምህርት ሥራ ለመሥራት ያልተፈቀዱ ዲጂታል ወይም AI ተጠቅመው ከሆነ ውጤት ለመስጠት፣ የአካዳሚክ ሐቀኝነት የጎደለው ድርጊት ላይ እምነት መጣል አይችሉም።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች 2026